ዕለታዊ የፕሬስ ገለፃ
ሻን ማክኮርማክ፣ ቃል አቀባይ
ዋሽንግተን፣ ዲሲ
ጥቅምት 22 ቀን 1998

የቃል አቀባይ መግለጫ

ሁሉም ፓርቲዎች አሁኑኑ አፋጥነው ታጋሽነትን በማሳየት ከከረረው የፖለቲካ ውጥረት ሁኔታ ወደ ኋላ እንዲያፈገፍጉና የኢትዮጵያ መንግሥትም በደርዘን የሚቆጠሩ ሰዎች የተገደሉባቸውን የዛሬውን ሕዝባዊ ትዕይንት እና በሰኔ 2 ቀን 1997 የተደረገውንም ሕዝባዊ ትዕይንት መንስዔ የሚያጣራ ነፃ ኮሚሽን እንዲያቋቁም እንጠይቃለን፡፡

ለፖለቲካ ልዩነቶች መፍትሔ ለማስገኘት በሚሞከር የተሳሳተ አካሄድ ሳቢያ በኃይል መጠቀምን እና ሌሎችም በኃይል እንዲጠቀሙ ሆን ብሎ ማነሳሳት ያሳዝኑናል፡፡ ሐሳባችንና ጸሎታችን በዚህ ቅጥ ያጣ በኃይል መጠቀም የተነሣ ሕይወታቸው ለተቀጠፉ ቤተሰቦች ነው፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት የፖለቲካ ታጋቾችን በሙሉ በቅርብ ሳምንታት ውስጥ በብዛት የታሠሩትን የተቃዋሚ ፓርቲዎች ደጋፊዎችን ጭምር፣ እንዲፈታ እንጠይቃለን፡፡ ዛሬ ተይዘው የታሠሩት፣ የተቃዋሚ ፓርቲ ከፍተኛ መሪዎች በሰብዓዊነት እንዲያዙ፣ ክስ የሚመሠረትባቸው ከሆነም ከአድሎዓዊነት ነፃ በሆነ ፍርድ ቤት ትክክለኛና ጊዜውን የጠበቀ ዳኝነት እንዲሰጣቸው ይገባል፡፡

ተቃዋሚውም ወገን በዚህ ውጥረት እጅግ ከፍ ባለበት ወቅት ሕዝቡ እምቢተኛ እንዲሆን ከማነሳሳት እንዲቆጠብ እንጠይቃለን፡፡ ሰላማዊ ተቃውሞ ለማድረግ መቻል በዲሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ ሕጋዊ መብት ቢሆንም፣ በፀበኝነት የታጀቡ ትዕይንቶች በሕዝብ ደህንነት ላይ ከፍተኛ አደጋን ከሚያስከትሉ በቀር ደሞክራሲን ወደፊት ለማራመድ አንዳች ፋይዳ አይፈጽሙም፡፡ ኢትዮጵያ ወደፊት እንድትራመድ ለማድረግ ጥሩው አማራጭ የፖለቲካ ቡድኖች ሁሉ፣ ከተቃዋሚ ወገን ለፓርላማና ለአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የተመረጡት አባላት ጭምር፣ በዲሞክራሲያዊው ሂደት ሙሉ ተሳትፎ ሲያደርጉ መሆኑን የአሜሪካ መንግሥት ያምናል፡፡